# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 312 ሚያዝያ 24 2006

**ግንቦት 7 የወያኔን አያያዝ አይተን የሁሉአቀፍ የአመጹን መንገድ ተከትለናል። ፈልገን ሳይሆን ተገደን በወያኔ ምርጫ የተመረጠልንን።**

**የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ወያኔ የህግና የሰላም በሩን ሁሉ ዘግቶ የተወልህን እና ሊከለክልህ የማይችለው ምርጫ የራስህን የነጻነት ትግል የአመጽ ሃይል ብቻ ነው። በየአለህበት በእምቢተኝነት ተነሳ!! መብትህንና ክብርህን ከወያኔ መጠበቅ የዋህነት ነውና ተነስ ተቀላቀል! ራስህን ነጻ አውጣ።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ጭፍጨፋውና አፈናው ይቁም፤ ወያኔ ይወገድ!!!

(የግንቦት 7 መግለጫ)

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲንቅናቄ፣ ዘረኛው ወያኔ በኦሮሚያ ሕዝብና ወጣቶች ላይ እያካሄደው ያለውን አረመኔያዊ ጭፍጨፋ፣ እስርና አፈናን በጥብቅ ይቃወዋል። ህወሓት፣ ኦህዴድ እና በዚህ ጭፍጨፋ እጃቸው ያለበት ሁሉ ከተጠያቂነት የማያመልጡ መሆኑን ያስገነዝባል።

የኦሮሚያ ወጣቶች በአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ስም የድሀ ገበሬዎች መፈናቀልን መቃወማቸው ፍትሀዊ ነው። የወያኔ “ማስተር ፕላኖች” የወያኔ የዘረፋ እቅዶች መሆናቸው በተደጋጋሚ የታየ ጉዳይ ነው። ነዋሪዎቹን ያላማከረ፣ ግንባር ቀደም ባለጉዳዮችን ባለቤት ያላደረገ፣ የሕዝብ ይሁንታ ያላገኘ ማስተር ፕላን ተፈፃሚ ማድረግ አይቻልም።

ወያኔ ኦሮሚያን ብቻ ሳይሆን መላዋን ኢትዮጵያ በምስለኔዎቹ አማካይነት እየገዛ የኢትዮጵያን ውድ ልጆች በራሳቸው ጉዳይ ባይተዋር አድርጓቸዋል። ኦህዴድ በወያኔ ቅጥረኛነት የኦሮሚያ ወጣቶችን በማስጨፍጨፍ ላይ ያለ እኩይ የአድርባዮች ስብስብ ነው። ወጣቶች የተቃወሙት ይህንን ነው።እነዚህ ወጣቶች በአካባቢያቸው ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በመላው ኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባቸዋል። ድምፃቸው ሊሰማ ይገባል። የሌላው አካባቢም ወጣት የኦሮሚያ ገበሬ መፈናቀል ያገባዋል። ኢትዮጵያዊያን በኢትዮጵያ ውስጥ በሚደረግ ጉዳይ ሁሉ ያገባናል። በየትኛውም የኢትዮጵያ ክልል ውስጥ ወያኔ የራሱን እቅድ እንዲጭንብን አንፈልግም። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## በገንዳሆ ከተማ በህዝቡና በፖሊስ መካከል በተፈጠረ ግጭት 4 ሰዎች ተገደሉ

ከላይ ከአናቱ አስከታች እግሩ ድረስ በሙስና ላይ የተገነባዉ የወያኔ ስርዐት ከገንዝብና ንብረት ዘረፋዉ ወጥቶ አንዳንድ አባላቱ ገንዝብ ያልሰጣቸዉን ዜጋ መግደል መጀመራቸዉን ከሰሜን ጎንደር የደረሰን ዜና ያስረዳል። ከዘሞኑ በሰሜን ጎንደር ዞን መተማ ወረዳ ዉስጥ የገንዳሆ ከተማ አንድ በጉምሩክ ፖሊስ ባልደረባ የሆነ የፌደራል ፖሊስ አንዱን የባጃጅ ሹፌር ”ኮንትሮባንድ ጨርቅ ጭነሃልና ጉቦ ሰጥተኸኝ እለፍ” በማለቱና ሾፌሩም “ለዚህ ለማይረባ ጨርቅ ጉቦ አልከፍልህም” የሚል መልስ በመስጠቱ ፖሊሱ ሾፌሩን ተኩሶ መግደሉን የአካባቢው ነዋሪዎች ለኢሳት ገልጸዋል።በድርጊቱ የተበሳጨው የገንዳውሃ ህዝብ ወደ ወረዳው ፖሊስ ጣቢያ በመሄድ ገዳዩ ለፍርድ እንዲቀርብ ጠይቋል። የወረዳው ፖሊስ ጽ/ቤትም “ጉዳዩ እኛን አይመለከትም ወደ ፌደራል ፖሊስ ሄዳችሁ ጠይቁ” የሚል መልስ መስጠቱን ነዋሪዎች ተናግረዋል።ህዝቡ ወደ ፌደራል ፖሊስ ጽ/ቤት በሚሄድበት ጊዜ፣ ፖሊሶች በከፈቱት ተኩስ 3 ሰዎች ወዲያውኑ ሲገደሉ፣ 3 ሰዎች ደግሞ በጽኑ ቆስለው ወደ ጎንደር ሆስፒታል ተወስደዋል።

ገንዳሆና አካባቢዉ ዉስጥ ውጥረቱ አሁንም እንዳለ ሲሆን፣ የአካባቢው ህዝብ ግድያዉንና የመንግስትን ቸልተኝነት አስመልክቶ የሚያካሄደዉ የተቃውሞ ሰልፍ እንደቀጠለ መሆኑን ከስፍራዉ የሚደርሱን ዜናዎች ያስረዳሉ። የወረዳው መስተዳድር በያዝነዉ ሳምንት ዉስጥ ህዝቡን ሰብስቦ ያነጋገረ ሲሆን፣ ህዝቡ ከዚህ በሁዋላ ከመንግስት ጋር አንተባበርም ማለቱን የአካባቢው ሰዎች ተናግረዋል። አንዳንድ የድርጅቱ አባላት ሳይቀሩ ራሳቸውን ማግለላቸውን ያነጋገርናቸው ሰዎች ገልጸዋል። ውጥረቱ አሁንም ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ሕወሃት መረጋጋት እያጣ እንደሆነ ተጠቆመ

ሁሉንም መንቀሳቀሻ መንገዶች በመቆጣጠር ወይም አፍኖ በመያዝ እንጅ በመወያየት የሚገኝን የሃሳብ የበላይነት የማይቀበለው ሕወሃት ተጨማሪ ጋዜጠኞችንና ጦማሪያንን በማሰር ሰሞኑን የሚታማበትን ያለመረጋጋት ችግር እያረጋገጠ እንደሆነ ተጠቆመ። በኢንተርኔት አማካኝነት የሚገኙ መገናኛ መንገዶችን በመዝጋት፣ የኢንተርኔት ካፌ ባለቤቶችን በማስፈራራትና ቁጥራቸውንም በመቀነስ በዚህ መንገድ የሚገኘውን አገልግሎት እጅግ በጣም ደካማ ያደረገው ወያኔ፤ በዚህ በደከመው መገናኛ መንገድ ተጠቅመው ሃሳባቸውን ማስተላለፍ የቻሉትን ስድስት ጦማሪያንን ጨምሮ ሶስት ጋዜጠኞችን ዘብጥያ ማውረዱ ብዙዎችን እያነጋገረ ነው።

ከፍተኛ የስለላ መሳሪያ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በመግዛት በግንቦት 7 አመራሮችና ራሱ በሚጠረጥራቸው የራሱ የወያኔ ሰዎች ላይ በመግጠም መረጃ ሲሰበስብ እንደነበር የተጋለጠበት ሕወሃት፤ ይህን ሁሉ አድርጎም የሕዝብን እንቅስቃሴ ማቆም የተሳነው ይህ ጠባብ ቡድን የህን ሁሉ ችግር ተቋቁመው ሃሳባቸውን በድብቅ ሳይሆን በጠራራ ፀሐይ ሲያስተላልፉ የነበሩ ጋዜጠኞችን በማሰር ከፍርሃቱ ትንሽ ተንፈስ ያለ መስሏል።

የታሰሩት ጋዜተኞችና ጦማሪያን በእለተ ሰንበት በወያኔው ካንጋሮ ፍርድ ቤት የተሰጣቸውን በሚያነቡና በሚናገሩት የሕወሃት ምስል ዳኞች ፊት የቀረቡ ሲሆን እንደተለመደው ማህበራዊ መገናኛ መንገዶችን በመጠቀም ሕዝብን ለማተራመስ በውጭ ከሚገኙ የመብት ተሟጋች ሃይሎች ጋር ተመሳጥረው ሰርተዋልና የመሳሰሉትን ክሶች አቅርቧል ፋሽስት ወያኔ። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የወያኔ አልሞ ተኳሾች አምቦ ዉስጥ ከ30 በላይ ሰላማዊ ሰልፈኞችን ገደሉ

ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙትን የኦሮሞ ገበሬዎች ከመሬታቸዉ እያፈናቀሉ በልማት ሰም መሬቱን ለራሳቸዉና ለደጋፊዎቻቸዉ መቀራመት መጀመራቸዉ ያበሳጫቸዉ በየክልሉ በሚገኙ ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች ዉስጥ የሚገኙ የኦሮሞ ተማሪዎች የተቃዉሞ ሰልፍ ማድረጋቸዉን ተከትሎ በተፈጠረዉ ፍጥጫ አምቦ ዉስጥ ስምንት ተማሪዎችን ጨምሮ ከሰላሳ በላይ ሰላማዊ ስልፈኞች መገደላቸዉን ከተለያዩ የአገር ዉስጥና የዉጭ ምንጮች የተገኘዉ ዜና የስረዳል። ከአዲስ አበባ ካርታ ጋር በተያያዘ የኦሮሞ ተማሪዎች የሚያሰሙት ተቃውሞ በድሬዳዋና አዳማ ዩኒቨርስቲዎች የቀጠለ ሲሆን፣ በአምቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትም ግጭቱ መቀጠሉንና በርካታ ተማሪዎች መታሰራቸው ታውቋል።

በድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የተቃውሞ ሰልፍ ለማድረግ እንዲፈቀድላቸው ቢጠይቁም፣ በግቢያቸውን ውስጥ ተቃውሞ ለማድረግ ተገደዋል። ይህንን ተከትሎ ዩኒቨርስቲውን የወረረው የፌደራል ፖሊስ በርካታ ተማረዎችን ደብድቦ ብዙዎችን ደግሞ ወደ እስር ቤት ልኳቸዋል። በአዳማ ዩኒቨርስቲም እንዲሁ ተማሳሳይ ተቃውሞ እየተካሄደ ነው። ከኦህዴድ ታማኝ ምንጮች ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው ከትናንት በስቲያ ምክር ቤቱ እስከ እኩለ ሌሊት ባደረገው ስብሰባ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ተማሪዎችን መስለው የሚገቡ የደህንነት ሰዎች ተመልምለው መረጃዎችን እንዲሰበስቡና እንቅስቃሴውን እንዲቆጣጠሩ ውሳኔ አሳልፏል። የፌደራል ፖሊሶች በቀጥታ የሃይል እርምጃ የሚወስዱት ተቃውሞው ከዩኒቨርስቲ ግቢ ወጥቶ ህዝቡን እንዳይጨምር በመስጋት መሆኑን ምንጮች አክለው ተናግረዋል። ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ወያኔ ያገታቸዉ የሰማያዊ ፓርቲ ወጣት አመራሮችና ደጋፊዎች በዋስ አንፈታም አሉ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛሰዝ በራሱ እጅ የጻፈዉ ህገ መንግስት በግልጽ ለህዝብ የሰጠዉን መብት በመጠቀም የተቃዉሞ ሰልፍ ለማድረግ በዝግጅት ላይ የነበሩትን የፓርቲውን ምክትል ሊ/መንበር አቶ ስለሺ ፈይሳንና የህዝብ ግንኙነት ሃላፊውን ብርሃኑ ተክለያሬድን ጨምሮ ከ20 በላይ አመራሮችና ደጋፊዎች ይዞ ማሰሩ የሚታወስ ነዉ። እነዚህ ወያኔ በግፍ ያሰራቸዉ የሰማያዊ ፓርቲ መሪዎችና አባላት ፍርድ ቤት ቀርበው በነበረበት ወቅት ፣ ፍርድ ቤቱ ፖሊስ ክስ እንዲመሰርት ወይም እስረኞቹ በዋስ እንዲለቀቁ ቢያዝዝም ታሳሪወቹ ግን የፍርድ ቤቱን ሃሳቡ እንደማይቀበሉት ለፍርድ ቤቱ አሳዉቀዋል። እስረኞቹ “ሰልፉ ህጋዊ እውቅና አግኝቶ በመገናኛ ብዙሃንም የተዘገበ በመሆኑ ፖሊስ ህገወጥ ሰልፍ አድርገዋል በሚል ለፍርድ ቤቱ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም፣ በነጻም ልንፈታ ይገባል” በማለት ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ኢትዮጵያ በህግ አምላክ የሚባልባት ሀገር መሆኗ ቀርቷል

ግፈኛውና ዘራፊው የወያኔ መንግስት በኢትዮጵያ መሬት ከሚሰራቸው ትልልቅ ወንጀሎች አንዱና ምናልባትም ዋነኛው በህግና ሕገ-መንግስት ላይ የሚያካሄደው ቀልድና ጭዋታ ነው። ሕገ-መንግስት ህዝብን ከእብሪተኛ መንግስት መጠበቂያ መሳሪያ መሆኑ ቀርቷል። ህግና ሕገ-መንግስት ለወያኔ ሲፋጅ በማንኪያ ሲበርድ በጣት የሚበላ ነገር ነው። ወያኔና አፋኝ ስርአቱ ህግ የሚጠቅሱት ለራሳቸው ይጠቅመናል ባሉበት ሰዓት ነው። ህግ ለነሱ ካልተመቻቸው ተቀዶ የሚጣል ቆሻሻ ወረቀት ነው።

በኢትዮጵያ ምድር ዋናው ሕገወጥ ተቋም ራሱ ላወጣው ሕግ የማይገዛው ወያኔ/ ህወሃት ነው። ለዚህ ነው "ለሚመለከተው አካል ከማሳወቅ ውጪ ሰላማዊ ሰልፍ ለማካሄድ ፈቃድ አይጠየቅም" የሚለውን ራሱ ያወጣውን ህግ ጥሶ ሰሞኑን ተቃዋሚዎችን ቁም ስቅላቸውን የሚያሳያቸው። ለዚህም ነው ሃሳብን በጽሁፍና በቃል ለመግለጽ ቅድመ ምርመራ እና እገዳ አይኖርም ብሎ ጽፎ፣ አለም አቀፍ የሰበአዊ መብት ድንጋጌዎች እንዳሉ ተቀብያለሁ ብሎ የተናገሩና የጻፉ ሰዎችን የሚያሳድደውና በሽብርተኝነት የሚከሰው።

ኢትዮጵያ "በሕግ አምላክ" የሚባልባት ሀገር መሆኗ ቀርቷል። ወያኔ ይህን ለህግ ትልቅ ክብር ያለውን የህዝባችንን የዘመናት እምነት ድራሹን በማጥፋት ላይ ይገኛል። ፍትህ በወያኔ አፋኞች መዳፍ እጅ ወድቃለች።

በዚያ አስከፊ የደርግ መንግስት ስርአት እንኳን ዳኞችን "እንዲህ ብላችሁ ፍረዱ" የሚል ትእዛዝ አልነበረም።

ዛሬ በየፍርድ ቤቱ አለም እየታዘበ የሚከናወን አይን አውጣ አሰራር እና የህወሃት የንጹሃን ዜጎችን የፖለቲካ መቀጣጫ ቤት ሆኖ ተለምዶል። ፍትህ እና ፍርድ ቤት እንዲዋረድ ሆኗል። ፍትህና ዳኝነት ራሱ በህወሃት የታሰረበት ጊዜ ነው።

ባለፈው ሳምንት ወያኔ አፍሶ ማእከላዊ በማስገባት የሚያሰቃያቸው የዞን 9 የኢንተርኔት ፌስቡክ ተጠቃሚዎች በሀገሪቱ ህገ መንግስት ከተለመደው መሰረታዊ መብታቸው ውጪ ያደረጉት ቅንጣት ወንጀል የለም። ወያኔ በፈራ እና በደነገጠ ቁጥር ሺህ ህግ ይጥሳል፡፡ ወያኔ ደግሞ ጥላውን የሚፈራ ድንጉጥ ተቋም ነው።

የኢትዮጵያን ህዝብ እንደ ጠላት እንጂ እንደ አብሮ ኗሪ ዜጋ ማየቱን ከተዎ የሰነበተውም ለዚህ ነው።
ዛሬ ራሱ ወያኔም እኛም በሕግና በሕጋዊነት ላይ ያለን ተስፋ ተሟጧል። ስለዚህም ነው ምርጫችን ይህን ህገ ወጥ የወንበዴ መንግስት በትጥቅ አልባም ይሁን በታጠቀ ሁለገብ አመጽ ማስወገድ ብቻ ነው የምንለው።

ግንቦት 7 የወያኔን አያያዝ አይተን የሁሉአቀፍ የአመጹን መንገድ ተከትለናል። ፈልገን ሳይሆን ተገደን በወያኔ ምርጫ የተመረጠልንን።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ወያኔ የህግና የሰላም በሩን ሁሉ ዘግቶ የተወልህን እና ሊከለክልህ የማይችለው ምርጫ የራስህን የነጻነት ትግል የአመጽ ሃይል ብቻ ነው። በየአለህበት በእምቢተኝነት ተነሳ!! መብትህንና ክብርህን ከወያኔ መጠበቅ የዋህነት ነውና ተነስ ተቀላቀል! ራስህን ነጻ አውጣ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## ጭፍጨፋውና አፈናው ይቁም፤ ወያኔ ይወገድ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ የኦሮሞ ወጣቶች ጥያቄ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ አድርጎ እንዲወስድ ጥሪ ያደርጋል። በጉራፈርዳና በቤንሻንጉል የተጀመረው መፈናቀል ዛሬ አዲስ አበባ አጎራባች ከተሞች ደርሷል። በአምቦ ይህንን የተቃወሙ ወጣቶች በግፍ ተጨፍጭፈዋል፤ በሌሎች ቦታዎችም ላይ ግድያውና እስሩ በርትቷል። ወጣቱ የጥይት እራት ሆኖ እስኪያልቅ መጠበቅ አንችልም፤ ሁሉም ትግሉን ይቀላቀል።

የወያኔ የጥቃት ሰለባ የሆኑት የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ጉዳይን ያነሱ ወጣቶች ብቻ አይደሉም። በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የወያኔን አምባገንነት የተቃወሙ በሙሉ የጥቃቱ ሰላባዎች ናቸው። ለሰልፍ ቅስቀሳ አደረጋችሁ በሚል የታሰሩ የሰማያዊ ፓርቲ ወጣቶች ሰልፉ ተደርጎ ካለቀ በኋላም አልተፈቱም።

ሀሳባቸውን በቲዩተር እና ፌስ ቡክ ማኅበራዊ ሚዲያዎች ሲገልጹ የነበሩ የዞን ዘጠኝ አባላት በአሸባሪ ድራማ በታጀበ ትዕይንት ወደ ማሰቃያ ሥፍራ ከተወሰደ ቀናት ተቆጥረዋል።

ይህ ሰቆቃ ማብቃት አለበት። ጭፍጨፋውና አፈናው ይቁም፤ ወያኔ ይወገድ!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

---

## ሕወሃት መረጋጋት እያጣ እንደሆነ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ከዚህ በፊት በሃሳብ ያልተስማሙአቸውን የራሳቸውን የወያኔ ባለስልጣናት እንዴት አድርገው ከሰው ዘብጥያ እንዳወረዳቸው በማስታወስ የሚጀምሩት ታዛቢ "እነዚህ ሰዎች በስልጣን ላይ እስከቆዩ ድረስ የፈለጉትን ማድረግና ያሻቸውን ማግኘት ይችላሉ ስለሆነም ከስልጣን በቀር ሌላ የሚያስቡትም ሆነ የሚመኙት ነገር የለም። ሰሞኑን በመላ ሀገሪቱ የሚታየው አለመረጋጋትና ከፍተኛ እንቅስቃሴ ደግሞ ከዚህ ከምንም በላይ ከሚመኙት ስልጣናቸው እንዳያስወግዳቸው ስጋት ብቻ ሳይሆን ጭንቀት ውስጥ ከቷቸዋል ስለሆነም ያልተጠናና ያልታሰበ እርምጃ ሲወስዱ እያየን ነው።"

"ራሳቸው ወያኔዎች ባመጡብን ጣጣ የተነሳ በድንበር ማካለል ሰበብ እሰጥ አገባ ውስጥ የገቡትን የሶማሌና አፋር ክልሎችን ምክንያት በማድረግ የወያኔ ፌደራሎች ስንቱን ገድለው ምን ያህሉን እንዳቆሰሉ ዓለም እያየ ነው። ከአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ጋር በተያያዘ ጥያቄ እያነሱ ያሉ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ የተወሰደው ጭካኔ የተሞላበት እርምጃም ሕወሃት ለኋሙ እንደተለቀቀ ፈረስ እንዳሻው ሲሆን እንደነበር አረጋግጧል። ከዚያ እጅግ ሲከፋ ደግሞ ተደብቀው ሳይሆን በግልጽ በችግር ውስጥ ሆነው ሃሳባቸውን ለማስተላለፍ ሲሞክሩ የነበሩ ጋዜጠኞችንና ጦማሪዎችንን ዘብጥያ አውርደዋል። ራሳቸው የፈቀዱትን ሰልፍ እንዳንሳተፍ እንኳ ስንት ተንኮልና ማስፈራራት ሲያደርሱብን ነበር። አሁን እኮ ሕወሃት የራሳቸውን የስልጣን ወንበር ለማዳን እንኳ በመመካከር እየሰሩ አይመስለኝም። በፍጹም የእውር ድንብር ጉዞ ሆኗል" በማለት ሲታዘቡ የሰነበቱትን በስፋትና በምሬት ገልጸዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሂውማን ራይትስ ወች የተባለው ለሰብአዊ መብት መከበር የቆመው ተቋም ስድስቱ ጦማሪዎችና ሶስቱ ጋዜጠኞች ባስቸኳ እንዲፈቱ መጠየቁ ተሰምቷል። ሕወሃት አሁንም ሃሳባቸውን በነጻነት ለማስተላለፍ የሚሞክሩና ተቺ ጋዜጠኞችን ማፈኑን እንደቀጠለ ነው ያለው የድርጅቱ መግለጫ፤ የሰሞኑ እስር የዩናትድ ስቴትስ ውጭ ጉዳይ ሚንስትር ጆን ኬሪ ሀገሪቱን ለመጎብኘት ቀናት ሲቀሩት መፈጸሙ ወያኔ ለመናገር ነጻነት ያለውን የተንጋደደ አቋም ያሳያልም ብሏል።

ከዚህ በፊት የነበረውን የሕወሃትን አካሄድ የሚያስታውሱ ታዛቢዎች ግን "ሕወሃት እርዳታ ከሚያፈሱለት ምእራባዊያን ሀገሮችም ሆነ ከሰብአዊ መብት ተንከባካቢ አካላት እየደረሰበት ያለውን መገለልና ውግዘት ወደ ነበረበት ቦታ ለመመለስና እንዲሁም እነዚሁ አካላት እየጠየቁት ያለውንና በሀገሪቱ እንዲታይ የሚፈልጉት የመልካም አስተዳደር እና የዴሞክራሲ እጦት ባጠቃላይ የሁሉን አቀፍ መሰረታዊ ለውጥ ጥያቄ ጉዳይ እንዳይነሳ ለማድረግ የሰሞኑን ታሳሪዎች ለመደራደሪያነት ሊጠቀምባቸው ይችላል ይላሉ። ፋሽስት ወያኔ ከዚህ በፊት የሚፈራቸው ዋና ዋና ጥያቄዎች ከእርዳታ ጥገቶቹ ምእራባዊያን በኩል እንዳይነሱበት ለማድረግ የሸፋን እርምጃዎችን ቀድሞ በመውሰድ እንደሚደራደር ይታወቃል።

---

## የትግል አቅጣጫውን ያላወቀ እና በማእበል ላይ ያለ ጀልባ አንድ ናቸው!!

( ዮሴፍ )

ህወሃት ወያኔ በተደናገጠ ወይም በበረገገ ቁጥር አዲስ ነገር ይዞ ብቅ ማለቱ የተለመደ ነው። በተለይም ህዝብ ከህዝብ ከፋፍሎ እና አጋጭቶም ሆነ ከትውልድ ስፋራው እያፈናቀለና እየገደለም ቢሆን የስልጣነ መንበሩን መነቃነቅ ባሸተተ ቁጥር ሁሌም ዛሬም ነገም ከዚህ አደጋ የሚወጣበትን መንገድ መፈልፈሉ የሚታወቅ ሃቅ ነው። እንደ 40/60 ኮንዶሚኒየም አሁን በተለይም በቅርብ ጊዜ ካየናቸው የፖለቲካ ትግሉን አቅጣጫ ለማስለወጥ ሞቹ አምባገነኑ መለስ ዜናዊ በአንድ ጀምበር ከተኙበት ባነው "አባይን መገደብ አለብን ህዝቤ ሆይ ተከተለኝ፣ አባይን የደፈረ... ብላችሁም ዘምሩልኝ" በሚል የአረቡ አለም የነጻነት አቢዎት በግብጽ፣ ሊቢያ እና ቱኒዚያ የተጀመረው አምባገነኖችን ጠራርጎ የወሰደው የነጻነት ወራጅ ውሃ እንዳይወስደው ግድብ ሊያበጅለት ዘንድ የአባይን ሳይሆን የነጻነት ጩኸትን ሊገድብ ዘዴ ፈጠረ። በዚህም የዲያስፖራውንና የሀገሩን ውስጥ ህዜብን ይህ እኮ ሀገራዊ ጉዳይ ነው በፖለቲካ ብንለያይ በአባይ ላይ ግን አንድ ነን በሚል ብልጣብልጥ ዘዴ ንጹሃንን የሚያስርበት፣ የሚገድልበት ገንዘብ ነገር ግን በአባይ ስም ልመና ሞከረ አልተሳካም እንዴውም በውጪ ለስብሰባ አዳራሽና ለባለስልጣኑ ትራንስፖርትና ሌሎች ተጨምረው ያወጣቸው ብሮች ለስራው ቢውል የተሻለ ነበር በሚል የውስጥ ወቀሳም ደረሰበት። ታዲያ ለጊዜውም ቢሆን survive ለማድረግ በመምሰል ቢንገዳገድም የገባበት አላማ ለእውነተኛ ግድብ ባለመሆኑ ዛሬ አለም አቀፍ ባለሙያዎች "ጥናት ያልተደረገበት ነውና ይደረግ" በሚል ሙያዊ ልገሳቸውን ቢሰጡም ይህን ችላ ብሎ ለሀገር ተቆርቋሪ በመመስል በሁሉም ዘርፍ የተጀመረበትን የትግሉን አቅጣጫ ለማስቀየር አሁንም እየሞከረ ነው።

በአንጻሩ ለሱዳን በጎንደር መተማ የነጻነት ሃይሎች የእምቢተኝነት ድምጻቸውን፣ ጉልበታቸውን አጠናክረው እንዳይመጡበት እጅ መንሻ ይሆን ዘንድ እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር ስምምነት አደረግን በሚል May 21, 2008 መለስ ዜናዊ መሬት ለሱዳን መሰጠቱን እንዲህ ሲል ነገረን We, Ethiopia and Sudan, have signed an agreement not to displace any single individual from both sides to whom the demarcation benefits. We have given back this land, which was occupied in 1996. This land before 1996 belonged to Sudanese farmers. There is no single individual displaced at the boarder as it is being reported by some media. አቶ ስዩ አብርሃ በአንድ ወቅትም ይህ መሬት መሰጠቱን ለቪ.ኦ.ኤ ጋዜጠኛ እውነት መሆኑን አረጋግጠዋል። አሁን ደግሞ ሃይለማርያም ደሳለኝ ቀጠሉበት። መከረኛ አማራው በየሄደበት መሬቱን እየለቀቀ እንዲሰደድም አደረጉ። ታዲያ ይህ እንግዲህ በጣም ቀላሉ ማንም የሚያውቀውን እውነት ነው።

ስለዚህ ይሄን ዘረኛ ሀገራዊ ራእይ የሌለው ቡድን ሁሌ በየጊዜው በሚሰጠን አጀንዳ እየታለልን ለምን የትግል መስመራችንን እንስታለን? ፖለቲከኞች የሚታገሉለትን እና የሚታገሉበትን ዘዴ በትክክል ይዘው ካልሄዱ፣ ባለሙያዎችም ይህን ተረድተው ብእራቸውን አስተካክለው መታገል ያለባቸውን ካላወቁ አውቀነውም ሆነ ሳናውቀው ለወያኔ የትግል ዘዴ እየተመቻችን ነው። ለዚህ አባባሌ ምክንያት የሆነኝ ሰሞኑን እነ ዶ/ር ሚንጋ ነጋሽ፣ ፕሮፌሰር ማሞ እና ዶ/ር ስይድ ስለ አባይ የጻፉት Misplaced Opposition to the Grand Ethiopian Renaissance Dam" ጽሁፍ ነው። በእኔ እምነት 50+ የሆነው ኢትዮጵያዊ ግድቡን አይቃወምም ነገር ግን መቅደም የሚገባውና መገደብ ያለበት የወያኔ የጥይት አፈሙዞች የሚተፋትን እሳት ነው። በመሆኑም ተቃዋሚው ጎራ የአባይ አጀንዳ የመጣው ለማደናበር መሆኑን በደንብ በተረዳበት ሰአት፤ በታቃዋሚው ጎራ የሚታወቁት ግለሰቦች ወያኔ እንኳን ከልቡ መገደብ ሳይፈልግና ብሄራዊ ተቆርቋሪ መስሎ ለመቅረብ ያሰበውን አጀንዳ ተቀብሎ ማጨብጨብ የትግሉን አቅጣጫ ማስለወጥ ተገቢ አይደለም። ሰሞኑን እንኳን ሰላማዊ ሰልፈኞችን ወደ 30 የሚያህሉ ንጹሃንን የገደለ መንግስት እንዴት ሆኖ ነው ብሄራዊነት የሚሰማው? እናም ብእራችሁ ማእበል ላይ ሆኖ መወዛዎዝ የለበትም። እናንተ የጻፍችሁት ጽሁፈ-ጥናት የወያኔ መንግስት የውጪ አምባሳደሮች ወይም የኢትዮጵያ ኢምባሲ በአሜሪካ ዌብሳይት ወይም አይጋ ፎረም ላይ የሚለጠፍ ጽሁፍ ሆኖ ነው ያገኘሁት። ስለዚህ በኢትዮጵያ ህዝብ እና ሏኡላዊነት የሚደርሰውን በደል ማስቀደም ከተማሩ ፖለቲከኞች የሚጠበቅ ነው። መጻፋችሁ ጥሩ ነው ነገር ግን እኛ እናንተን የምናውቃችሁ ደግሞ በተቃዋሚነት ነውና በማእበሉ ተናውጣችሁ ካልተቀየራችሁ በስተቀር እናንተ የኢትዮጵያን ልጆች ሃብት ናችሁ እና እባካችሁ የትግሉን አቅጣጫ አትለውጡት። የወገኖቻችሁ፣ የሀገራችሁ ህዝብ በመሬት ስንጠቃ፣ በግድብ ሰበብ ከቀዬው እየተፈናቀለ ነው እና ያንን እናተኩር። የዶ/ር አክሎግ ቢራራ ኢትዮጵያዊነትን አጥፍቶ አባይን መታደግ ይቻላልን? የሚለው ሙያዊ ገለጻ በሚገባ አስቀምጦታል። እርግጥም እንዳሉት ኢትዮጵያዊነትን አጥፍቶ አባይን መታደግ ይቻላልን? ባሉት ጽሁፋቸው "አባይ ፈንጅ የቀበረ ውሃ ነው"። እኛ የጠማን ውሃ ነው! እኛ ያጣነው መብራት ነው! ስለዚህ አባይ የኛ ነው!! ነገም ዛሬም ትላንትም! የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ለወያኔ የስልጣን መቆያ እንጅ መንሻ እንዲሆን አንፈልግም። ኢትዮጵያኖች በወያኔ አጅንዳ ውስጥ ገብተን አንዋኝም። አጥቂዎች እንጂ ተከላካዮች አይደለንም። እናም ግድ የለም እናንተ የምትሉትን እነሱው ካወቁበት በዲፕሎማሲ ቋንቋ በተለመደ ውሸታቸው ይበሉት። እናንተ ግን የእኛ ናችሁ። ተሳሳትሁ እንዴ?

---

## ሰመራ፤ አምቦ፤ ድሬደዋና አዲስ አበባ - በየክልሉ ኢትዮጵያ በተቃዉሞ እየተናወጠች ነዉ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የሚወስዳቸዉን ፀረ ህዝብና ፀረ አገር እርምጃዎች በመቃዉም የኢትዮጵያ ህዝብ በየቦታዉ የሚያሰማዉን ተቃዉሞ በማጧጧፍ ላይ መሆኑን ከየክልሉ የሚደርሱን ዜናዎች ይጠቁማሉ። ይህ ዕድሜ፤ ሞያና ፆታን ያልለየና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ያጠቃለላ ህዝባዊ ተቋዉሞ በየትምህርት ቤቱ፤ በየከተማዉና በገጠር አካባቢዎች ከአፋር ሰመራ እስከ አምቦ፤ ከአዲስ አበባ እስከ ድሬደዋ የተካሄደዉ የተቃዉሞ ሰልፍ ወያኔን ክፉኛ በማስጨነቁ ይህ በገዳይነቱ ወደር የለሌዉ አገዛዝ እንደለመደዉ አልሞ ተኳሾችን ልኮ ከ30 በላይ ሰልፈኞችን ገድሏል። ሆኖም ከሃያ ሦስት አመታት በላይ የወያኔን በደል የተሸከመዉ የኢትዮጵያ ህዝብ የወያኔን የግድያ ዘመቻ ከምንም ባለመቁጠር የተቃዉሞ ሰልፉን እንገፋበት ለማወቅ ተችሏል።

የአፋር ክልል መስተዳደር መቀመጫ በሆነችዉ ሰመራ ዉስጥ ከሰሞኑ በተካሄደ የተማሪዎች ተቃውሞ የልዩ ሃይል አባላት በተማሪዎች ላይ ድበደባ ፈጽመዋል። ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ ተማሪዎች ተደብድበው ሆስፒታል ሲገቡ በርካታ ቁጥር ያላቸው ደግሞ ታስረዋል። የኮሌጅና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ጧት ላይ መኪኖችን አግደው ከዋሉ በሁዋላ ልዩ ሃይል በወሰደው እርምጃ እገታውን ቆሟል። ተማሪዎች ከሰአት በሁዋላ ወደ ክልሉ ጽህፈት ቤት በመሄድ ተቃውሞአቸውን ሲያሰሙ ውለዋል። ተማሪዎች ግድያው እንዲቆምና የሰብአዊ መብታቸው እንዲከበሩ የሚጠይቁ መፈክሮችን አሰምተዋል።በተቃውሞ ሰልፉ ላይ የተገኘውን አንድ ተማሪ በቀጥታ አግኝተን አነጋገርነዋል። የፍትህ ቢሮ ሃላፊው ተማሪዎች ተወካዮችን መርጠው እንዲልኩ ለማግባባት ቢሞክሩም ተማሪዎች ግን የሃላፊውን ምክር ለመቀበል ፈቃደኞች ሆነው አልተገኙም።ካለፈው ቅዳሜ ጀምሮ በአፋር ክልል የተነሳው ተቃውሞ እየተጠናከረ መምጣቱን ነዋሪዎች ይናገራሉ። የፌደራል ፖሊስ ከ8 እስከ 12 የሚደርሱ የአፋር ተወላጆችን መግደሉን መዘገባችን ይታወሳል።

ከአዲስ አበባ ካርታ ጋር በተያያዘ የኦሮሞ ተማሪዎች የሚያሰሙት ተቃውሞ በድሬዳዋና አዳማ ዩኒቨርስቲዎች የቀጠለ ሲሆን፣ በአምቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትም ግጭቱ መቀጠሉንና በርካታ ተማሪዎች መታሰራቸው ታውቋል።በድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የተቃውሞ ሰልፍ ለማድረግ እንዲፈቀድላቸው ቢጠይቁም፣ በግቢያቸውን ውስጥ ተቃውሞ ለማድረግ ተገደዋል። ይህንን ተከትሎ ዩኒቨርስቲውን የወረረው የፌደራል ፖሊስ በርካታ ተማረዎችን ደብድቦ ብዙዎችን ደግሞ ወደ እስር ቤት ልኳቸዋል።በአዳማ ዩኒቨርስቲም እንዲሁ ተማሳሳይ ተቃውሞ እየተካሄደ ነው። ከኦህዴድ ታማኝ ምንጮች ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው ከትናንት በስቲያ ምክር ቤቱ እስከ እኩለ ሌሊት ባደረገው ስብሰባ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ተማሪዎችን መስለው የሚገቡ የደህንነት ሰዎች ተመልምለው መረጃዎችን እንዲሰበስቡና እንቅስቃሴውን እንዲቆጣጠሩ ውሳኔ አሳልፏል።የፌደራል ፖሊሶች በቀጥታ የሃይል እርምጃ የሚወስዱት ተቃውሞው ከዩኒቨርስቲ ግቢ ወጥቶ ህዝቡን እንዳይጨምር በመስጋት መሆኑን ምንጮች አክለው ተናግረዋል።በመሆኑ መሰረተ ሃሳቡን ጭምር አጥብቀው ይቃወሙታል።

................................................................................................

## ወያኔ ጋዜጠኞችንና ጦማሪያንን ሰብስቦ እስር ቤት መወርወሩ ተሰማ

ሀሳብን በነጻነት መግለጽ ከሚለዉ ሀሳብና ከጋዜጠኞች ጋር ዕድሜ ልኩን ሆድና ጀርባ የሆነዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ከዉጭ ኃይሎች ጋር በመመሳጠር አለመረጋጋት ፈጥራችኋል ያላቸዉን ኢትዮጵያዉያን ጋዜጠኞችና ጦማሪያን ይዞ ማሰሩንና ረጂም ዘመን በሚያሳስር ከፍተኛ ወንጀል ለመክሰስ የተለመደ የዉሸት ማስረጃ በመሰብሰብ ላይ መሆኑን ከአዲስ አበባ የደረሰብ ዜና ያስረዳል። ይህ ከሰሞኑ መላዉን አለም ያንጫጫዉ የወያኔ እስር ስድስት ጋዜጠኖችንና "ዞን 9" በመባል የሚታወቁትን ብሎገሮች ያጠቃልላል። ይህንን አይን ያወጣ የወያኔ እስር ወያኔ ከዚህ ቀደም ከፈጸማቸዉ ዔትየለሌ እስሮች ልዩ የሚያደርገዉ እስሩ የተፈጸመዉ የአሜሪካዉ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጆን ኬሪ አዲስ አበባ ሊገቡ ጥቂት ቀናት ሲቀራቸዉ መሆኑ ሲሆን በተለይ አንደኛዉ ታሳሪ ባለፈዉ አመት ጆን ኬሪ አዲስ አበባ በነበሩበት ወቅት አግኝተዉ ያናገሩት ጋዜጠኛ መሆኑ ነዉ። አስራ ሰባት አመት ተዋግቼ የኢትዮጵያ ህዝብ ለረጂም አመታታ የተጠማዉን ነጻነትና ዲሞክራሲ እንዲገነጭ አድርግያለሁ እያለ የሚፏልለዉ የወያኔ መንጋ እግሩ አዲስ አበባን ከረገጠበት ግዜ ጀምሮ ምንም ሳይቀይር በተከታታይ የደረገዉ ነገር ቢኒር የነጻ ፕሬስ አባላትን ማሰር፤ ጋዜጠኞችን ማስር እንዲሁም ሀሳባቸዉን በነጻነት የገለጹ የህብረተሰብ አባላትን ማሰር ነዉ። ይህ ተግበሩ ደግሞ ወያኔን "ነጻነትን የማያዉቅ የነቀነት ተዋጊ" የሚል የተቀጢላ ስም እንዲያገኝ አድርጎታል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ወያኔ ወያኔ ወንጀለኞች  ናቸዉ ብሎ ያሰራቸዉን ጋዜጠኞች ዓለማቀፉ የጋሴጠኞች ተንከባካቢ ድርጅት(ሲፒጄ) በአስቸኳይ እንዲፈቱ ጠይቋል። ድርጅቱ የጋዜጠኞቹን መታሰር አስመልክቶ ባወጣዉ መግለጫ የኢትዮጵያ መንግስት ሰሞኑን በ9 ጸሀፍያን ላይ የወሰደው የእስር እርምጃ፤ ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ላይ ከተቃጡ የከፉ እርምጃዎች አንዱ ነው ብሏል።"የኢትዮጵያ ባለስልጣናት በሰላማዊ መንገድ ሀሳብን መግለጽን እንደወንጀል እየቆጠሩት ነው" በማለት ነው -የሲፒጄ የምስራቅ አፍሪቃ ወኪል-ቶም ሩድስ-እርምጃውን የኮነኑት።

እሁድ ዕለት የመንግስት አቃቤ ህግ በ አዲስ ጉዳይ ዋና አዘጋጅ በ አስማማው ሀይለጊዮርጊስ፣ በፍሪላንስ ጋዜጠኞቹ በተስፋለም ወልደየስ እና በ ኤዶም ካሣዬ፣ እንዲሁም በጦማርያኑ በ አቤል ዋቤላ፣በ አጥናፍ ብርሀኔ፣በማህሌት ፋንታሁን፣ በዘላለም ክብረት እና በበፈቃዱ ሀይሉ ላይ ከውጪ ድርጅቶች ጋር ይሠራሉ፣ ማህበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀምም በሀገሪቱ አለመረጋጋት እንዲፈጠር ይንቀሳቀሳሉ.. የሚል ክስ እንደመሰረተባቸው ሲፒጄ አውስቷል።ተስፋለም፣አስማማውና ዘላለም ለፊታችን ሚያዚያ 28 ቀሪዎቹ ደግሞ ለሚያዚያ 29 እንደተቀጠሩ ከሀገር ውስጥ ጋዜጠኞች የደረሰውን መረጃ ዋቢ አድርጎ የጠቀሰው ሲፒጄ፤ በታሳሪዎቹ ላይ እስካሁን መደበኛ ክስ እንዳልተመሰረተ ጠቁሟል።

ሲፒጄ በመግለጫው-ፀሀፊዎቹ ዞን ዘጠኝ ተብሎ የሚጠራ የገለልተኛ አክቲቪስቶች ስብስብ አባል ሆነው የተለያዩ ዜናዎችንና ጽሑፎችን ይጽፉ እንደነበር አመልክቷል። "ዞን ሰጠኝ የተሰኘው ስያሜ ከቃሊቲ የተገኘ መሆኑና የጸሐፊዎቹ መሪ ቃል፡-"ስለሚያገባን እንጦምራለን" የሚል መሆኑ በሲፒጄ መግለጫ ተመልክቷል። ጦማርያኑና ጋዜጠኞቹ የታሰሩት ከደህንነቶች በሚደርስባቸው ወከባ ምክንያት ላለፉት ሰባት ወራት ዘግተውት የቆዩትን የፌስቡክ ገፃቸውን ዳግም በከፈቱ ማግስት መሆኑን እንደተረዳም የጋዜጠኞች መብት ተንከባካቢ ተቋሙ ገልጿል። ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማርያም ደሳለኝ አማካሪ የሆኑት ጌታቸው ረዳ ለሮይተርስ የዜና ወኪል፡- "የታሰሩት ጋዜጠኞች አይደሉም፤ እስሩ ከጋዜጠኝነት ሥራቸው ጋር የተገናኘ አይደለም። ከከባድ ወንጀል ጋር የተገናኘ ነው" ማለታቸውን ሲ.ፒ.ጄ ጠቁሟል። "በጋዜጠኝነት ወይም ሀሳብን በነጻ የመግለጽ መብት ላይ የቃጣነው በትር የለም። ሆኖም ማንም ቢሆን ሙያውን ሽፋን በማድረግ ወንጀል ለመፈፀም ሲሞክር በህግ ይጠየቃል" ሲሉም አክለዋል-አቶ ጌታቸው ረዳ።

"የኢትዮጵያ ባለስልጣናት ወደለየለት ፈላጪ ቆራጭ አገዛዝ ማዘንበላቸውን እንዲገቱና በሀገሪቱ ነፃ ሀሳቦች ይንሸራሸሩ ዘንድ እንዲፈቅዱ ጥሪ እናቀርባለን" ብለዋል-ሚስተር ቶም ሩድስ። የታሰሩት 9ኙም ጸሀፊዎች በአስቸኳይ ሊፈቱ ይገባል ሲሉም ጠይቀዋል። ዓለማቀፉ የሰብዓዊ መብት ተቋም ሂውማን ራይትስ ዎችና ሌሎች ድርጅቶችም የኢትዮጵያ ባለስልጣናት በጦማርያኑ እና በጋዜጠኞቹ ላይ የወሰዱትን እርምጃ በማውገዝ ፤ ኢትዮጵያን ለመጎብኘት ዛሬ አዲስ አበባ የሚገቡት የ አሜሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ጆን ኬሪ እስረኞቹን እንዲፈታ በኢትዮጵያ መንግስት ላይ ግፊት እንዲያደርጉ ጠይቋል። የተለያዩ ዓለማቀፍ የሚዲያ ተቋማትም ሰሞኑን የኢትዮጵያ መንግስት በ9ኝ ጦማርያን እና ጋዜጠኞች ላይ የወሰደውን የማሰር እርምጃ ሽፋን ሰጥተውታል።ከሚዲያ ተቋማቱ መካከል ኤ.ቢ.ሲ ኒውስ፣ ሲ ኤን.ኤን፣ ዋሽንግተን ፖስት፣ ሬውተርስ፣ እና አልጀዚራ ይገኙበታል። እንዲሁም የዩናይትድ ስቴትስ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ጆን ኬሪ በጉብኝታቸው ስለታሰሩት ጦማርያን እና ጋዜጠኞች አጠንክረው እንደተናገሩ የኒውዮርክ ታይምሱ ታዋቂ አምደኛ ኒኮላስ ክሪስቶች ለሰጣቸው አስተያዬት፤ " በጣም ጠቃሚ ጉዳይ ነው። ዩናይትድስቴትስ በመላው ዓለም ላይ የፕሬስ ነፃነትን በመደገፍና ከጥቃት በመከላከል ባላት ጠንካራ አቋም ትቆያለች" በማለት ምላሽ ሰጥተውታል።

## ኢትዮጵያ የታሰሩ ጋዜጠኞችና ጸሃፊዎችን እንድትፈታ ሂውማን ራይትስ ወች ጠየቀ

የኢትዮጵያ መንግስት ተጨባጭ ማስረጃ እስካላመጣ ድረስ በህገወጥ መንገድ ያሰራቸውን 3 ጋዜጠኞችና 6 ጦማሪያን በአስቸኳይ እንዲፈታ የሰብአዊ መብት ድርጅቱ አሳሰበ፡፡ ኢትዮጵያን የሚጎበኙት የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ተጠሪ ጆን ኬሪ ፍትሃዊ ባልሆነ ዳኝነት በእስር የሚሰቃዩ ጋዜጠኞች እንዲሁም ያለበቂ ማስረጃ የሚታሰሩት ጋዜጠኞች እና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች እንዲፈቱ በኢትዮጵያ መንግስት ላይ ጫና እንዲያሳድሩ ሂውማን ራይትስ ወች ጠይቋል። የሂውማን ራይትስ ወች የአፍሪካ ዳይሬክተር ሌስሌ ሌፍኮ "የ9ኙ ሰዎች መታሰር መንግስትን የሚተቹ ሁሉ አፋቸውን እንዲዘጉ እንደሚደረጉ ማሳያ ነው" ብለዋል። ዞን 9 እየተባለ የሚጠራ የፌስ ቡክ አካውንት በመክፈት ጽሁፎችን ሲጽፉ ከነበሩት ወጣቶች መካከል በፈቃዱ ሃይሉ፣ አጥናፍ ብርሃኔ፣ ናትናኤል ፈለቀ፣ ማህሌት ፋንታሁን፣ ዘላለም ክብረት እና አቤል ዋቤላ ከስራ ቦታቸውና ከመንገድ ላይ ታፍሰው መታሰራቸውን፣ ጋዜጠኛ ተስፋ አለም እና ኤዶም ካሳየም እንዲሁ ፖሊስ ወደ ማእከላዊ እስር ቤት ተወስደው መታሰራቸውን ድርጅቱ ገልጿል። የአዲስ ጉዳይ መጽሄት ዋና አዘጋጅ አስማማው ሃይለ ጊዮርጊስም እንዲሁ ወጣቶቹ በታሰሩ ማግስት መታሰራቸውን በመግለጫው ጠቅሷል። በእስር ላይ የሚገኙት ወጣቶች ከማንም ጋር እንዳይገናኙ ተደርጎ የታሰሩ በመሆኑ ለጥየቃ የሄዱ ቤተሰቦች ሳያገኙዋቸው ቀርቷል።

ዞን 9 እየተባሉ የሚጠሩ ወጣቶች ከዚህ ቀደም ተደጋጋሚ የሆነ ማስፈራሪያ ሲደርስባቸው ነበር። ሂውማን ራይትስ ወች የኦባማ አስተዳደር በኢትዮጵያ ስለሚታየው የሰብአዊ መብት ጥሰት ምንም አለማለቱን ወቅሷል። የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች መድረክ (ኢጋመ) ባወጣው መግለጫ ደግሞ መድረኩ እስካሁን በሰበሰበዉ መረጃ መሰረት ወጣቶቹን ለእስር የሚያበቃ ምን ም አይነት ማስረጃ ለማግኘት አለመቻሉን ገልጿል። ለእስር ከመዳረጋቸው በፊት ከመንግስት ሲርስባቸዉ በነበረዉ ህገወጥ ድርጊቶች ምክንያት ለረጅም ጊዜ ስራቸዉን ካቋረጡበኋላ በቅርቡ ወደ ስራ መመለሳቸዉን ይፋ አድርገው እንደነበር ከድረገጻቸው ላይ ለመረዳት መቻሉን ኢጋመ ጠቅሷል።የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች መድረክ መንግስት ታሳሪዎቹን ለማሰር ያበቃዉ ተጨባጭ ማስረጃ ካለ ለህዝብ ይፋ እንዲያደርግ፤ ያ ካልሆነ ግን እስረኞቹን በአስቸኳይ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲለቅ ጥያቄ አቅርቧል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ለገዢው ፓርቲ ቅርበት አለው የሚባለው ዛሚ ኤፍኤም 90.7 ከዞን 9 ጋር በተያያዘ የታሰሩ ጸሃፊዎችና ጋዜጠኞች ላይ የተጀመረው እስር በሌሎችም ላይ እንደሚቀጥል የሚያረጋግጥ ዘገባ አቅርቧል፡፡

ሬዲዮው ከፖሊስ ታማኝ ምንጮቼ አገኘሁት ባለው መረጃ መሠረት ከዞን 9 ጋር በተያያዘ የታሰሩ ብሎገሮችና ጋዜጠኞች በህቡዕ ተደራጅተው መንግስትን በአመጽ ለመጣል ማሴራቸውን፣ እንዲሁም ማናቸውንም ዓይነት ሰላማዊ ሰልፎች እንዲካሄዱና በሰልፎቹ ላይ መንግስትን ለመቃወም ስልጠናዎችን በውጪና በአገር ውስጥ መውሰዳቸውን አትቷል፡፡

እንደዘገባው ከሆነ ጤናን የሚመለከት ሰልፍም ቢሆን እንዴት ወደተቃውሞ መቀየር እንደሚቻል ተጠርጣሪዎቹ ስልጠና መውሰዳቸውን ተናግራል፡፡ ሬዲዮው ከታሰሩት በተጨማሪ በሕጋዊ መንገድ በመመስረት ሒደት ላይ የሚገኘው ኢትዮጵያ የጋዜጠኞች መድረክ (ኢጋመ) በተመሳሳይ መንገድ በውጪ አገር ከሚንቀሳቀሱ ተቋዋማት ጋር ግንኙነት እንዳለው ከፖሊስ መረጃ አግኝቻለሁ ከማለቱም በተጨማሪም በማህበሩ ላይ ፖሊስ ክትትል እያደረገ መሆኑን ገልጿል፡፡ ይህ ሁኔታ በቀጣይ ማህበሩ ላይ ትኩረት መደረጉን እንደሚያሳይ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ጠቁመዋል፡፡

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ  የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

<u>መካከኛ ሞገድ</u>፡- በ 358 MB, በ 837 kHz
አ<u>ጭር ሞገድ</u>፡- በ 31 MB  በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና  በ 7120** KHz
**በ 49 MB በ  5980** KHz **እና  በ 60 MB  4760** GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።
<u>ማሳሰቢያ</u>፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## በገንዳሆ ከተማ በህዝቡና በፖሊስ መካከል በተፈጠረ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

እንዳለ ሲሆን ፖሊሶች አመጹን አስነስተዋል የተባሉትን ወጣቶች ይዘው ማሰራቸውም ነዋሪዎች ተናግረዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የአቡነ ሃራ ቤተክርስትያን አገልጋይ የሆኑት ቄስ መልካሙ ማስረሻ በጎንደር ማራኪ በሚባለው አካባቢ ከሚታየው ቤት ማፍረስ ጋር ተያይዞ ቤታቸው የሚፈርስባቸውን ሰዎች በመወከል እስከ ክልል መስተዳደር ድረስ በመሄድ አቤቱታ ሲያሰሙ ከቆዩ በሁዋላ ፣ ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች ተገድለው መገኘታቸውንና ትናንት የቀብራቸው ስነስርአት መፈጸሙ ታውቋል።

ቄስ መልካሙ ” መንግስት መጀመሪያ ሰዉ ቤት ሲሰራ በንዝህላልነት ዝም ብሎ ስንት እና ስንት ጉልበት እና ገንዘብ ከወጣ በኋላ ይፍረስ ብሎ ማለቱ አላግባብ እና ህዝብን መናቅ ነው” በማለት በተደጋጋሚ ይተቹ ነበር። በዚህ አቋማቸው የተነሳ ህዝቡ መብቱን እንዲያስከብሩለት ወክሏቸው በተደጋጋሚ ወደ ክልሉ ርዕሰ ከተማ ተጉዘው አቤቱታ አሰምተዋል።

ነገር ግን ከሶስት ቀን በፊት ቤተክርስትያን በአስቸኳይ ትፈለጋለህ ተብሎ ማንነታቸው ባልታወቀ ሰዎች ከተጠሩ በኋላ ተገድለው ተገኝተዋል። ኢሳት ከአንድ ወር በፊት ቄስ መልካሙን አነጋግሮቸው ነበር። በጊዜው መንግስት ጉዳዩን በጽሞና እንዲያየው ተማጽኖ አቅርበው ነበር። ለትውስታ ይሆን ዘንድ ቄስ መልካሙ በጊዜው የሰጡትን አጭር ቃለምልልስ እነሆ ይህ በእንዲህ እንዳለ በጎንደር አዘዞ አካባቢ ጋብ ብሎ የነበረው ቤት የማፍረሱ እርምጃ ዛሬ ተጀምሯል። የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት የህዝቡ ወኪሎች ተቃውሞ ለማሰማት ይፈቀድላቸው ዘንድ ዛሬ ወደ መስተዳደር በሚሄዱበት ጊዜ ተይዘው ታስረዋል።

## የወያኔ አልሞ ተኳሾች አምቦ ዉስጥ ከ30 በላይ ሰላማዊ ሰልፈኞችን . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የመስተዳድሩ ባለስልጣናት ያወጡትን የከተማዋን አዲስ ማስተር ፕላን ተከትሎ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች የሚገኙ የኦሮሞ ተወላጆች የጀመሩት ተቃውሞ ወደ ተለያዩ ዩኒቨርስቲዎችና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመዛመት ላይ ነው። በአምቦ ቁጥራቸው በውል ያልታወቁ ተማሪዎች በፌደራል ፖሊሶች ሲገደሉ በድሬዳዋ ደግሞ በመቶዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎች ታስረዋል። በአዳማ የተጀመረው ተቃውሞ የረገበ ቢመስልም ውጥረቱ ግን አሁንም እንዳለ ነው።

ይህ በእንዲ እንዳለ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የ6 ኪሎ ተማሪዎች ተቃውሞ ለማድረግ እንቅስቃሴ በጀመሩበት ወቅት የዩኒቨርስቲው ሃላፊዎች ተማሪዎችን አነጋገርው ተቃውሞውን ጋብ እንዲል አድርገውታል። የክልሉ ባለስልጣናት በነገው እለት ተማሪዎችን ያነጋግራሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ ለማወቅ ተችሎአል። በግንደ በረት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ባስነሱት ተቃውሞም እንዲሁ በርካታ ተማሪዎች ተጎድተዋል። ተማሪዎች አርሶደሮችን ከመሬታቸው በህገወጥ መንገድ ማፈናቀሉ እንዲቆም እየጠየቁ ሲሆን፣ የመንግስት ባለስልጣናት በበኩላቸው እቅዱ በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉ አርሶ አደሮች ከልማቱ ተጠቃሚ ይሆናል በማለት ህዝቡን ለማሳመን እየጣሩ ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የአሜሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ሚስተር ጆን ኬሪ አዲስ አበባ በገቡበት ዕለት በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኤምባሲ ከአዲስ አበባ እና ኦሮሚያ የጋራ የማስተር ፕላን ጋር ተያይዞ በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የተቀጣጠለውን ተቃውሞ መነሻ በማድረግ አሜሪካዊያን በተለይ ወደ አምቦ አካባቢ እንዳይጓዙ መግለጫ አውጥቷል። ኢምባሲው በአምቦ የተነሳውን ከፍተኛ ተቃውሞ ተከትሎ ወደ አካባቢው የሚሄዱ አሜሪካውያን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አሳስቧል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ግንቦት7 የፍትህ ፣ የነጻነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ የመንግስት የጸጥታ ሃይሎች በኦሮሞ ሕዝብና ወጣቶች ላይ እያካሄደው ያለውን አረመኔያዊ ጭፍጨፋ፣ እስርና አፈናን በጥብቅ አውግዟል። ህወሓት፣ ኦህዴድ እና በዚህ ጭፍጨፋ እጃቸው ያለበት ሁሉ ከተጠያቂነት የማያመልጡ መሆኑንም ገልጿል።“የኦሮሚያ ወጣቶች በአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ስም የድሀ ገበሬዎች መፈናቀልን መቃወማቸው ፍትህዊ ነው” ያለው ግንቦት7፣ የወያኔ “ማስተር ፕላኖች” የወያኔ የዘረፋ እቅዶች መሆናቸው በተደጋጋሚ የታየ ጉዳይ ነው ሲል አክሏል።

ወያኔ ኦሮሚያን ብቻ ሳይሆን መላዋን ኢትዮጵያ በምስለኔዎቹ አማካይነት እየገዛ የኢትዮጵያን ውድ ልጆች በራሳቸው ጉዳይ ባይተዋር አድርጓቸዋልሲል የሚኮንነው ግንቦት7፣ ወጣቶች በአካባቢያቸው ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በመላው ኢትዮጵያ ጉዳይ እንደሚያገባቸው፣ ድምፃቸው ሊሰማ እንደሚገባ ገልጿል።“የሌላው አካባቢም ወጣት የኦሮሚያ ገበሬ መፈናቀል እንደሚያገባው፣ ኢትዮጵያዊያን በኢትዮጵያ ውስጥ በሚደረግ ጉዳይ ሁሉ እንደሚያገባውና፣ በየትኛውም የኢትዮጵያ ክልል ውስጥ ወያኔ የራሱን እቅድ እንዲጭንብን አንፈልግም። ” ሲል አቋሙን አንጸባርቋል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ የኦሮሞ ወጣቶች ጥያቄ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ አድርጎ እንዲወስድም ጥሪ አድርጓል። ”በጉራፈርዳና በቤንሻንጉል የተጀመረው መፈናቀል ዛሬ አዲስ አበባ አጎራባች ከተሞች ደርሷል። በአምቦ ይህንን የተቃወሙ ወጣቶች በግፍ ተጨፍጭፈዋል፤ በሌሎች ቦታዎችም ላይ ግድያውና እስሩ በርትቷል። ወጣቱ የጥይት እራት ሆኖ እስኪያልቅ መጠበቅ አንችልም፤ ሁሉም ትግሉን ይቀላቀል።” ብሎአል።

በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የወያኔን አምባገንነት የተቃወሙ በሙሉ የጥቃቱ ሰላባዎች ሆነዋል የሚለው ግንቦት7፣ ለሰልፍ ቅስቀሳ አደረጋችሁ በሚል የታሰሩ የሰማያዊ ፓርቲ ወጣቶች ሰልፉ ተደርጎ ካለቀ በኋላም አለመፈታታቸውን ፣ ሀሳባቸውን በቲዩተር እና ፌስ ቡክ ማኅበራዊ ሚዲያዎች ሲገልጹ የነበሩ የዞን ዘጠኝ አባላት በአሸባሪ ድራማ በታጀበ ትዕይንት ወደ ማሰቃያ ሥፍራ ከተወሰዱ ቀናት መቆጠራቸውን” በመግለጽ ይህ ሰቆቃ ፣ ጭፍጨፋና አፈና ይቁም” ብሎአል።

አንድነት ፓርቲ ለኢሳት በላከው መግለጫም እንዲሁ በሰፊው የኦሮሞ ህዝብ እና ልጆች ላይ እየተፈፀመ ያለውን ግፍ በአጽንኦት እናወግዛለን ብሎአል።“ምንም አይነት ህዝባዊ ውይይት ሳይደረግበት ከሰማይ ዱብ ያለው የአዲስ አበባ እና ኦሮሚያ ልዩ ዞን የተቀናጀ የልማት መሪ ፕላን ያስቆጣቸው የኦሮሞ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሰልፍ በማድረጋቸው የደረሰባቸውን ህገ ወጥ ድብደባና እስራት” አንድነት በእጅጉ እንደሚቃወመው ገልጿል።

ተማሪዎቹ ለተቃውሞ አደባባይ ቢወጡ ተፈጥሯዊ እና ህገ መንግስታዊ መብታቸው ሊከበር በተገባ ነበር ያለው ፓርቲው፣ ነገር ግን ሁሉን ነገር ካልጋትኳችሁ የሚለውና ለዴሞክራሲያዊ ሽንፈት የማይገዛው ኢህአዴግ በተማሪዎቹ ላይ ያደረሰውን ጥቃት እንቃወማለን ብሎአል። የታሰሩ ተማሪዎችም በአስቸኳይ እንዲፈቱ፣ የኦሮሞ ተማሪዎችን በገፍ ከዩኒቨርሲቲ የትምህርቦ ገበታቸው በማባረር የሚታወቀው የኢህአዴግ መንግስት ከዚህ ተደጋጋሚ ተግባሩ ታቅቦ ልጆቹን በአስቸኳይ ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዲመልስም ጠይቋል።በአጠቃላይ መሬት የዜጎች መያዣ መሆኑ እንዲቀር እንታገላለን ያለው አንድነት፣ ዜጎች በመሬታቸው የመደራደር እውነተኛ መብት ሊኖራቸው እንደሚገባ ተቃውሞ የሚያነሱ ዜጎችም ድምፅ እንዲሰማም አሳስቧል።

## ወያኔ ያገታቸዉ የሰማያዊ ፓርቲ ወጣት አመራሮችና

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

መከራከሪያ በማቅረባቸው ምንም ውሳኔ ሳይሰጥበት ወደ እስር ቤት እንዲመለሱ ተደርጓል።

የአመራሮችና ደጋፊዎች መታሰር በተቃውሞ ሰልፉ ላይ ተጽእኖ ነበረው ወይ ተብለው የተጠየቁት የፓርቲው ሊቀመንበር ኢንጂነር ይልቃል፣ የመንግስት አፈና ተጽእኖ እንደነበረው ገልጸው፣ ይሁን እንጅ መረጃ የደረሰው ህዝብ ሰልፉን መቀላቀሉንና ድምጹን ማሰማቱን ገልጸዋል። “ፓርቲዎ የቀለም አብዮት ለማስነሳት እየሰራ ነው በሚል ከኢህአዴግ መንግስት ክስ ይቀርብበታል፣ ምልሽዎ ምንድነው?” ተብለው የተጠየቁት ኢ/ር ይልቃል፣ ፓርቲያቸው ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር እንዲኖር እንደሚፈልግ እና የቀለም አብዮት የማስነሳት እቅድ እንደሌለው ገልጸው፣ “ኢህአዴግ አገሪቱን መምራት ባለመቻሉ ግራ ተጋብቶ፣ እሱም የማይወደውን እኛም የማንወደውን እንድናደርግ እየገፋፋን ነው” ብለዋል።

ይህ በአንዲህ እንዳለ ለዳግማይ ትንሳኤ በዕቅድ ተይዞ የነበረዉ ሰማያዊ ፓርቲ የጠራዉ የተቃዉሞ ሰልፍ የወያኔ ፖሊሶችና የጸጥታ ሀይሎች ህዝቡን በሰልፉ ላይ እንዳይገኝ የተቻላቸዉን ያክል ማስፈራራያና ወከባ ቢያደርጉም ህዝብ ወከባዉንና ማስፈራሪያዉን ከምንም ባለመቁጠር በሰላማዊ ሰልፉ ላይ ተካፋይ ሆኗል። የፓርቲዉ የህዝብ ግኑኝነት ዘርፉ ሃላፊ በሰተዉ መግለጫ መሰረት የአዲስ አበባ መስተዳድር እውቅና የሰጠዉና በጃንሜዳ የተካሄደው የተቃውሞ ሰልፍ ህዝቡ ሀሳቡንና ከወያኔ ጋር አብሮ ለመጓዝ ፈቃደኛ አለመሆኑን የገለጸበት የተሳካ ሰልፍ ነበር ብሏል።

ወጣት ብርሃኑ እንዳለው የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽነር በሰልፉ ላይ አንድም ነገር ቢከሰት እንዲሁም ከተሰጣችሁ ጊዜ አንድ ማይክሮ ሰከንድ ብታልፉ ሰልፉን እንበትናለን በማለት ለማስፈራራት ሞክረዋል። ማስፈራሪያውን የሰጡት የፖሊስ አዛዡ በስም ይታወቁ እንዲሆን ጥያቄ የቀረበለት ወጣት ብርሃኑ፣ ኮሚሽነሩ ማንነቱን የሚገልጽ መረጃ በጠረጴዛው ላይ ባለማስቀመጡ ስሙን ለማወቅ እንዳልተቻለ፣ ነገር ግን ቢሮው ውስጥ አብረው የነበሩትን ኮሚሽነር እንደሚያውቃቸው ገልጿል ቅስቀሳው በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ ና የህዝቡም ማበረታቻ ጥሩ መሆኑን የገለጸው ወጣት ብርሃኑ ፣ ነገር ግን በቅስቀሳ ላይ የነበሩ 25 አባሎቻቸው ታስረው እስካሁን አለመፈታታቸውን ገልጿል።ወጣት ብርሃኑ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ ግብ ሳይሆን ወደ ቀጣዩ ትግል መሸጋገሪያ መሆኑን ገልጾ ፣ የአዲስ አበባ ህዝብ በነቂስ ወጥቶ ድምጹን ያሰማል ብሎ እንደሚያምን ተናግሯል።